የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር ዘ3ኣ/ቁ61-7/598
Ref.
ቀን 28 መጋቢ 1997
Date

ለአዲስ አበባ ላጋር ጉምሩክ
አዲስ አበባ

በቁጥር አሳ60/አ51/1262 በ23/07/97 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የመኪና መለዋወጫ ዋጋን በተመለከተ የProportion አሠራር ግልጽ በሆነ መልኩ የተቀመጠ መመሪያ ያለመኖሩን በመግለጽ፣ በጣቢያችሁ የአሠራር ችግር በመፈጠሩና ሠነዶችም በጣቢያችሁ የሚገኙ በመሆኑ አፋጣኝ ማብራሪያ (መመሪያ) እንዲላክላችሁ ጠይቃችኋል።

በቁጥር ዘ20/ወ1/04 በ15/11/96 በዋና ሥራ አስኪያጅ በተፈረመ ሰርኩላር የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ከምችት አዘገጃጀት፣ ስርጭትና አጠቃቀም አስመልክቶ የወጣውን መመሪያ ለማስፈጸም የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/1996 ለመኪና መለዋወጫ አጠቃቀም እና ከፍተኛ የዋጋ ስጋት ካለባቸው አገሮች ለሚመጡ ዕቃዎች ጭምር በመመሪያው አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1-3 በተገለጸው መሰረት እንዲፈጸም እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ማሞ ሰንበቴ
የዋጋ ትመና ቡድን መሪ

አባሪ፣ ስሩት ገጽ

ግልባጭ፣
- ለታሪፍና ኦፕሬሽን ጉዳዮች ዘርፍ
- ለታሪፍና ዋጋ ጉዳዮች መምሪያ
  ጉምሩክ ባለሥልጣን

ፖ.ሣ.ቁ. P.O. Box 3248 ስልክ Tel. 51 31 00 ቴሌክስ Telex 21177 ፋክስ Fax 51 83 55
አዲስ አበባ Addis Ababa

15/11/96

2

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITY

16/11/96

[illegible] ቀጠናና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች

ጉዳዩ፦ <u>መመሪያ መላክን ይመለከታል</u>

የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት፣ አዘገጃጀት፣ ስርጭትና አጠቃቀም አስመልክቶ
ውን መመሪያ ለማስፈፀም የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/1996 እና በዋጋ ትመና
ች ላይ የሚነሱ አቤቱታዎችን ለመመልከት የሚችሉ የኮሚቴ አባላቶችን ለመወሰን
የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 3/1996 ቅጅ ያጠቃላለው 8 ገጽ ከዚህ ጋር አባሪ ተደርጎ
ክላችሁ ስለሆነ በአፈፃፀም መመሪያዎቹ በተገለፀው መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ
ታውቃለን።

ከሰላምታ ጋር

፡ 8 ገጽ

ግልባጭ፣
ለታሪፍና አፕሬሽን ጉዳዮች ዘርፍ
ለህግ ጉዳዮች ዘርፍ
ለታሪፍና ዋጋ ጉዳዮች መምሪያ
ለህግ መምሪያ
ለኦዲት አገልግሎት
ጉምሩክ <u>ባለስልጣን</u>
ለህዝብ ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት
ለጉምሩክ አስተላላፊዎች ሙያ ማህበር
ለጉምሩክ አስተላላፊዎች አሠሪዎች ማህበር
<u>አዲስ አበባ</u>

2

## የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት፣ አዘገጃጀት፣ ስርጭትና አጠቃቀም አስመልክቶ የወጣውን መመሪያ ለማስፈፀም የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/1996

1. አውጪው ባለሥልጣን

የጉምሩክ ባለስልጣን በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት አዘገጃጀት ስርጭትና አጠቃቀም የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 10/1996 አንቀፅ 27 ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

2. አጭር ርዕስ፡

መመሪያ "የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት አዘገጃጀት ስርጭትና አጠቃቀም አስመልክቶ የወጣውን መመሪያ ለማስፈፀም የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ የአፈፃፀም መመሪያ፡-

1. በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት አዘገጃጀት ስርጭትና አጠቃቀም የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 10/1996 ለተዘረዘሩት ቃላት የተሰጡት ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።
2. "አንድ ዓይነት ዕቃ" የሚለው ቃል በቅደም ተከተል
   - 2.1 በተመሳሳይ አገር በሌላ አምራች የተመረተ አንድ ዓይነት ዕቃን ይጨምራል።
   - 2.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2.1 ላይ የተመለከተውን ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ ሌላ አገር የተመረተ አንድ ዓይነት ዕቃን ይጨምራል።

[illegible] ደምስ

[illegible]

3. "ተመሳሳይ ዕቃ" የሚለው ቃል በቅደም ተከተል

3.1 በተመሳሳይ አገር በሌላ አምራች የተመረተ ተመሳሳይ ዕቃን ይጨምራል።

3.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3.1 ላይ የተመለከተውን ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ ሌላ አገር የተመረተ አንድ አይነት ዕቃን ይጨምራል።

4. "በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ አገሮች" ማለት በሚከተሉት ምድቦች ውስጥ የሚገኙ አገሮች ማለት ነው፡-

ሀ. አንደኛ ምድብ፡ የአውሮፓ አገሮች፣አሜሪካ(U.S.A)፣ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ጃፓን እና ኒውዚላንድ፣

ለ. ሁለተኛ ምድብ፡ ሁሉም የእስያ አገሮች(ከጃፓን በስተቀር)

ሐ. ሶስተኛ ምድብ፡ የላቲን አሜሪካ አገሮች፣

መ. አራተኛ ምድብ፡ የአፍሪካ አገሮች።

5. "መመሪያ" ማለት የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት አዘገጃጀት፣ ስርጭትና አጠቃቀም የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 10/1996 ነው።

6. "ጣቢያ" ማለት የጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያዎች ማለት ነው።

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ፡-

የገቢዎች ሚኒስቴር የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት፣አዘገጃጀት፣ስርጭት እና አጠቃቀምን አስመልክቶ የወጣውን መመሪያ በተሟላ፣ወጥ፣ በተብራራ እና ግልፅ በሆነ መንገድ ማስፈፀም ለማስቻል ነው።

## 5. የአንድ ዓይነት ዕቃ የዋጋ አወሳሰን

በገቢ ዕቃዎች የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ አወሳሰን ላይ ጣቢያው በዋጋ መረጃ ክምችት ውስጥ...

ዳምጠው ደምስ
ዋና ሥራ አስኪያጅ

1. በአንድ አምራች የተመረተ አንድ ዓይነት ዕቃ ዋጋ ማግኘት ካልተቻለ በዚያው አገር በሌላ አምራች የተመረተ የአንድ ዓይነት ዕቃ ዋጋ መውሰድ ይቻላል።
2. በዚያው አገር የተመረተ አንድ ዓይነት ዕቃ ዋጋ ማግኘት ካልተቻለ በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ አገር የተመረተ የአንድ ዓይነት ዕቃ ዋጋ መውሰድ ይቻላል።
3. የአንድ ዓይነት ዕቃ ዋጋ ከአንድ በላይ በሆኑ ተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ባላቸው አገሮች የሚገኝ ሲሆን ከፍተኛ ዋጋ ያለውን አገር ዕቃ ለዋጋ አወሳሰኑ መሰረት ይሆናል

## 6. የተመሳሳይ ዕቃ የዋጋ አወሳሰን

በገቢ ዕቃዎች የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ አወሳሰን ላይ ጣቢያው በዋጋ መረጃ ክምችት ውስጥ:-

1. በአንድ አምራች የተመረተ ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ማግኘት ካልተቻለ በዚያው አገር በሌላ አምራች የተመረተ ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ መውሰድ ይቻላል።
2. በዚያው አገር የተመረተ ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ማግኘት ካልተቻለ በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ አገር የተመረተ የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ መውሰድ ይቻላል።
3. የተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ከአንድ በላይ በሆኑ ተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ባላቸው አገሮች የሚገኝ ሲሆን ከፍተኛ ዋጋ ያለውን አገር ዕቃ ለዋጋ አወሳሰን መሰረት ይሆናል።

## 7. ከድብልቅ ማቴሪያሎች የተሰሩ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን

1. በመነሻ እና ማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ዋጋ የሚወሰንላቸው ዕቃዎች ከድብልቅ ማቴሪያል የተሰሩ ሲሆን፣ዋጋቸው ከድብልቅ ማቴሪያሉ ውስጥ አብዛኛውን እጅ በያዘው እና የዕቃውን ትክክለኛ ባህሪ በሚሰጠው ማቴሪያል ላይ በመመስረት ዋጋው ይወሰናል።

ዳምጠው ይምስ
ዋና ሥራ አስኪያጅ

## 10. የፍሬ ነገር መግለጫ /Declaration of facts/ አሞላል

1. በመመሪያው ላይ ተያይዞ በሚገኘው የፍሬ ነገር መግለጫ ቅፁ ላይ ስለ ዕቃዎች ዝርዝር አሞላል በተመለከተ የሚከተሉት መረጃዎች በሙሉ በቅደም ተከተላቸው መሰረት በጥንቃቄ ተሞልተው መቅረብ አለባቸው።

   ሀ. የዕቃው ስም፣

   ለ. የተሰራበት ማቴሪያል፣

   ሐ. ብራንድ እና/ወይም /የአምራች ስም/

   መ. ሞዴል ቁጥር/ፓርት ቁጥር

   ሠ. መጠኑ/Size/

   ረ. የጉልበቱ መጠን/Horse power, KW/

   ሰ. የአስተሻሸግ ሁኔታ/Packing/

   ሸ. የመረጃ ፋይል ስም፣ ቁጥር፣እና የመስመር ቁጥር

2. የሰው፣የእንስሳት እና የዕፅዋት መድሃኒቶችን በተመለከተ ከንግድ ስማቸው በተጨማሪ የኬሚካል ስማቸው መሞላት አለበት።

3. የመለዋወጫ ዕቃዎችን በተመለከተ ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመለዋወጫው ስም፣ የሚገጠምለት ተሽከርካሪ ዓይነት፣የፓርት ቁጥር በትክክል መሞላት አለበት።

4. የአዳዲስ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪው ስም፣ ሞዴል ቁጥር፣የሞተር ቁጥር፣የሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር ጉልበት እና የምርት ዘመን በትክክል መሞላት አለበት።

## 11. ልዩ ሁኔታ

1. የፌዴራል እና የክልል መንግስታት የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ አገር ለሚያስገቧቸው ዕቃዎች በሚያቀርቡት የዋጋ ኢንቮይስ መሰረት ጣቢያው ሊያስተናግድ ይችላል።

ዳምጠው ደምሴ
ዋ ሥራ አስኪያጅ

2. ጣቢያው ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያለውን አስመጪ እና/ወይም ዕቃ /Low risk importers and/or goods/ የዋጋ ልዩነቱ ከማነፃፀሪያ ዋጋ አንፃር ከ10 በመቶ ካልበለጠ ሊያስተናግድ ይችላል።

3. በመመሪያው አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ብቸኛ ወኪሎች የሚያስመጧቸው እና ለጉምሩክ የቀረበው የኤሌክትሮኒክስ እና የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች ዋጋ ከዓለም አቀፍ ገበያ ዋጋ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ልዩነት የሚታይበት ሆኖ ሲገኝ ከዓለም አቀፍ የመረጃ ምንጭ በሚገኝ ዋጋ መሰረት ጣቢያው ለመወሰን ይቻላል።

4. በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ በአንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች እስከተሟሉ ድረስ የዕቃው ዝርዝር ሁኔታ በሌሎች የንግድ ሰነዶች ውስጥ የተካተተ ከሆነ ዝርዝሩን በመረጃ መስጫ ዲክላራሲን ላይ መሙላት ሳያስፈልግ ዝርዝሩ የሚገኝበትን ሰነድ መጥቀስ ብቻ በቂ ሊሆን ይችላል።

## 12. ተጠያቂነት

ይህንን የአፈፃፀም መመሪያ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

## 13. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሃምሌ 12 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

ዳምጠው ደምስ
ዋና ስራ አስኪያጅ